የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

# የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር …. /2017.

ሐምሌ/ 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ለማንኛውም የተሸከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አስተዳደር ስርዓት ለመዘርጋት፤ የትራፊክ ፍሰትን ለማስተካከል፤ የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ፤ ፍትሃዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ያለው አሰራር እንዲኖር በማስፈለጉ፤

የትራንፖርትና ሎጅስቲክስ ሚ/ር የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 22 በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ " የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር.... /2017. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡

1. **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
2. **"ደንብ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር557/2016 ነው፡፡
3. በደንቡ አንቀጽ 2 ሥር የተሰጡ ሌሎች ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
4. **"አገልግሎት"** ማለት የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ማለት ነዉ፡፡
5. **‹‹የትራንስፖርት ቢሮ››** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ወይም የመንገድ ደህንነትን ወይም የመንገድ ትራፊክ አስተዳደር ሥራን ለመምራት ሥልጣን የተሰጠዉ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ነዉ፡፡
6. **"ክልል"** ማለት በኢትዮድያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡
7. **“ተሽከርካሪ”** ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የሚጠቀም ማንኛውም ባለሞተር ወይም ሞተር አልባ ተሽከርካሪ ነው፤
8. **“ምልክት እና ማመላከቻ”** ማለት በመንገድ እና ከመንገድ ውጪ በቁም የሚተከል ምልክት ወይም በመንገዱ ጠርዝ እና/ወይም በተሽከርካሪ መሄጃ መንገድ ላይ የሚቀባ ቀለም ነው፡፡
9. **“የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ”** ማለት አግባብ ባለው ህግ ወይም ፕላን መሰረት ለተሽከርካሪዎች ማቆሚያ እንዲውል በመንገድ ላይ እና ከመንገድ ውጪ የተለየ ስፍራ ነው፤
10. **“የመኖሪያ እና የንግድ አካባቢ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ”** ማለት አግባብ ባለው ህግ ወይም ፕላን መሰረት በመኖሪያ ቤቶች፣በካንፐ፣በንግድ ተቋማት ህንፃዎች እና አካባቢው ለተሽከርካሪዎች ማቆሚያ እንዲውል የተለየ ስፍራ ነው፤

11. **"ተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት"** ማለት ተሽከርካሪዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆሙበት ተብሎ በከተሞች ውስጥ የተዘጋጀ ወይም የተገነባ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ነው፤
12. **"ማህበራት"** ማለት የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማቶችን ለማስተዳደር በሚመለከተው አካል የስራ እድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ላይ በሚሰራ አካል በኩል ባለው አሰራር መሰረት የተደራጁ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ናቸው፤
13. **"የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት"** ማለት የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማቶችን ለማስተዳደር ወይም ለማልማት በሚመለከተው አካል በሚወጣው መስፈርት መሰረት ውል በመግባት በግለሰብ ወይም በንግድ ማህበር የመኪና ማቆሚያ አገልግሎት ለመስጠት እና ለማስተዳደር የተቋቋመ ድርጅት ነው፤
14. **" የሚመለከተዉ አካል"** ማለት በክልሎች ወይም ከተማ አስተዳድር የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማቶችን ለማስተዳደር የመፍቀድ ስልጣን ወይም ዉክልና ያለዉ የትራንስፖርት ቢሮ ነዉ፡፡
15. **"ተገልጋይ"** ማለት በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ላይ ተሽከርካሪ በማቆም አገልግሎት ያገኘ ማንኛውም ሰው ነው፤
16. **"የመንገድ ላይ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ"** ማለት በከተሞች በሚገኙ በተፈቀዱ መንገዶች ላይ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ እንዲሆኑ በምልክቶችና በቀለም የተለዩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ነው፤
17. **"የሕንፃ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ"** ማለት በህንፃ ህግ መሰረት ተሽከርካሪዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆሙበት በህንፃው ወይም በግቢው ውስጥ ከሕንፃው ጋር በተያያዘ ለሕንፃው ተገልጋዮች የተዘጋጀ ስፍራ ነው፤
18. **"የተሽከርካሪ ማቆሚያ ሕንፃ"** ማለት ለተሽከርካሪዎች ማቆሚያ ብቻ ተብሎ የተገነባና አገልግሎት የሚሰጥ ሕንፃ ነው፤
19. **"ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ"** ማለት ከዋና መንገድ ውጭ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ታስቦ የተዘጋጀ ቦታ ሆኖ ሜካኒካል ተደራራቢ ፎቅ ያለው ወይም ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረገ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ነው፡፡
20. **"የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት"** ማለት ከመንገድ ውጪ ያለ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ አገልገሎት እየሰጠ ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል የሚሰጥ ሰርተፊኬት ነው፤
21. **"የመንግስት መስሪያ ቤት"** ማለት በከፊል ወይም በሙሉ በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ እና የልማት ድርጅቶችን ይጨመራል፡፡
22. **"በመንግስት የለሙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች"** ማለት ማናቸውም በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ እና ከዋና መንገድ ውጪ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልገሎት የተገነቡ ወይም የተለዩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ናቸው፤
23. **"የተሽከርካሪ ማቆሚያ ግብዓቶች"** ማለት ውል ለገቡ ማህበራት ወይም ለግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅቶች እንደሁኔታው በክፍያ እና ያለክፍያ በሚመለከተው አካል የሚቀርቡ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ስርዓት መቆጣጠሪያ ታብሌቶች፣ ሰፍት ዌሮች፣የትራፊክ ምልክቶች፣የክፍያ መቀበያ ማሽኖች፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ

ደረሰኞች፣የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ማመላከቻ ቦርዶች እና ሌሎች መሰል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስርዓቱን ለማዘመን ወይም አሰራሩን ለማሻሻል የሚያገለግሉ ግብዓቶች ናቸው፡፡

24. **"የተሽካርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት ውል"** ማለት ማህበራት ከሚመለከተው አካል ጋር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎችን ለማስተዳደር የሚገቡት ውል ነው፤
25. **"የአገልግሎት ክፍያ"** ማለት የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የተጠቀመ ማንኛውም ተገልጋይ ላገኘው አገልግሎት የሚፈፅመው ክፍያ ነው፤
26. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
27. **በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡**

**3. ዓላማ**

በከተሞች ውስጥ የሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች በአግባቡ እንዲተዳደሩ በማስቻል የተሳለጠ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡

**4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በከተሞዎች ውስጥ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ፣ በአገልግሎት ሰጪ አካላት እና በተገልጋዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የተሽከርካሪ ማቆሚያ ዓይነቶች እና አስተዳደር

**5. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ዓይነቶች**

1. የመንገድ ዳር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ፤
2. ከመንገድ ውጪ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ፤

   ሀ. የህንፃ ላይ

   ለ. የህንፃ ስር

   ሐ. የመሬት ስር

   መ. የመሬት ላይ

   ሠ.ሌሎች ዘመናዊ የህንፃ ላይ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች

**6. የመንገድ ዳር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ፤**

1. የመንገድ ዳር ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ተብሎ በተሰራ መንገድ ላይ ወደ እግረኛ ጠርዝ በኩል ያለው እና ልዩ ምልክት የተደረገበት ነው፤
2. የመንገድ ላይ ምልክት እና ማመላከቻ ህጎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

ሀ. የሚመለከተው አካል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት የሚከፈልባቸው ስፍራዎችን በሚያወጣው የቀለም ስታንዳርድ መሰረት በመንገድ ጠርዝ ላይ ያመላክታል፤

ለ. አካል ጉዳተኛ ለሆኑ አሽከርካሪዎች ብቻ ለተሽከርካሪ ማቆሚያነት የተለዩ ቦታዎች ላይ የሚመለከተው አካል በመንገድ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ላይ በምስል ያመላክታል፤

ሐ. ዕቃ ለመጫን እና ለማውረድ በተለዩ መንገዶች ላይ የሚመለከተው አካል በመንገድ ጠርዙ ላይ በሚወጣው የቀለም ስታንዳርድ መሰረት ያመላክታል፤

መ. የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በተለየላቸው ማቆሚያ ስፍራ በነፃ የሚጠቀሙ ይሆናል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ምልክትና ማመላከቻ የተደረገባቸው አስገዳጅ የመንገድ ላይ ምልክቶች ናቸው፤
4. የሚመለከተው አካል በመንገድ ላይ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ተብለው በተፈቀዱ ቦታዎች ላይ ማህበራትን አሰማርቶ በክፍያ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፤
5. የሚመለከተው አካል የአካባቢውን የትራፊክ እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ የመንገድ ዳር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎችን በዘላቂነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነውን የመንገድ ክፍል ወይም አጠቃላይ የመንገድ ክፍል ምልክትና ማመላከቻ በማስቀመጥ ሊከለክል ወይም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

7 ከመንገድ ውጪ የሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች

1. ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዙ የመንገድ መስመሮች አቅጣጫ ጠቋሚዎች የጊዜ ሰሌዳ እና የአገልግሎት ተመኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ሊኖራቸው ይገባል፤
2. ማንኛውም ከመንገድ ውጪ ለሚገኝ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ተጠቃሚዎች የተለየ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

8.**ስለ ክፍያ**

1. **ከመንገድ ውጭ የሚገኙ የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት ስፍራ አገልግሎት ክፍያ ተመን ፍትሃዊነትን እና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎቱን በሚያቀርበው አካል የሚወሰን ይሆናል።**
2. **በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የተጋነነ አገልግሎት ክፍያ ሲኖር የሚመለከተው አካል አገልግሎት አቅራቢው ጋር በመነጋገር የአገልግሎት ክፍያ ስታንዳርድ ያወጣል።**
3. **የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ የሚሰጥ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት ለአካባቢዉ ነዋሪዎች ከክፍያ ነፃ ይሆናል፤**
4. **የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ክፍያን በተመለከተ የሚመለከተው አካል የአገልግሎት ክፍያ ጥናት በማድረግ ለመንግስት የፋይናንስ ቢሮ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤**

9. **ስለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አቅራቢዎች**

1. **የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት እና**
2. **በመንግስት የለሙ ተሽከርካሪ ማቆሚያዎች ናቸው።**

10. **ስለግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት አገልግሎት**

**የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት፦**

1. አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለአገልግሎት ብቁ ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት ሲችል ነው፤
2. የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ሙሉ ለሙሉ ለታለመለት ዓላማ ብቻ መዋል አለበት፤

11. በመንግስት የለሙ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች

በመንግስት የሚገነባ ከመንገድ ውጪ እና የመንገድ ዳር ተሽከርካሪ ማቆሚያ ሲሆን፡-

1. ማህበሩ ወይም የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅቱ በቅድሚያ ከሚመለከተው አካል ጋር የስራ ውል መግባት ይኖርበታል፤
2. ማህበራቱ ውል ከመግባታቸው በፊት አግባብ ባለው አካል በስራ መስኩ መሰማራት የሚችሉ ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤
3. የግል የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አቅራቢ ከሆነ ውል ከመዋዋሉ በፊት በቅድሚያ በአገሪቱ ህግ መሰረት አሸናፊ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል፤
4. የግል ወይም የማህበር የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አቅራቢ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በወጣው የክፍያ መጠን ይሆናል፤
5. በማህበር ወይም በግል የሚተዳደሩ በመንግስት የለሙ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ላይ ማህበሩ ወይም የግል አቅራቢው የመብራት፣የውሃ፣ የጽዳት እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎችን የሚሸፍን ይሆናል፤
6. ለገቢ መሰብሰቢያ የሚሆን ደረሰኝ በፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሰረት ለሚመለከተው አካል የሚያቀርብ ይሆናል፤
7. የሚመለከተው አካል በሚያወጣው የደንብ ልብስ ስታንዳርድ መሰረት ማህበራቱ ወይም የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅቶች ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ሰራተኞቻቸው አንፀባራቂ የደንብ ልስብ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤
8. የሚመለከተው አካል በመንግስት ለለሙ ተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎችንና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶችን የሚያቀርብ ይሆናል፤
9. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ቢኖርም እንደአስፈላጊነቱ የሚመለከተው አካል የክፍያ መሰብሰቢያ ቴክኖሎጂዎች እና ሌሎች ለስራ አስፈላጊ የሆኑ የግብዓት አይነቶችን ወስኖ ተዋዋዩ እንዲያቀርብ ሊያደርግ ይችላል።

**12. የተሽከርካሪ ማቆምያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬትስ ለማግኘት**

ማንኛውም በህንጻ ስር እና ህንጻ ዉስጥ የሚገኝ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለማግኘት የሚከተለትን ማሟላት አለበት፡-

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ደህንነቱ የተጠበቀ ወይም የህንጻ መጠቀሚያ ፍቃድ ያለው ስለ መሆኑ ከሚመለከተው አካል በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፤
2. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አስፈላጊ የሆኑ ምልክቶች፣አቅጣጫ ጠቋሚዎች፣ ክፍያ ላላቸው

ደረሰኝ፣የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያለው ባለሞያ፣ አስፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል እና የተሟላ የደንብ ልብስ፤

3. በግንባታ ዲዛይኑ መሠረት ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ሙሉ በሙሉ ለአገልግሎት ለማዋል ዝግጁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**13. የተሽከርካሪ ማቆምያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ስለሚሰጥበት ሁኔታ**

ማንኛውም የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ብቃት ማረጋገጫ የሚጠይቅ ሰው፡-

1. በሚመለከተው አካል የተዘጋጀውን ማመልከቻ ቅፅ መሙላትና መፈረም፤
2. አመልካች ድርጅቱ ወይም የመንግስት መስሪያ ቤቱ ማመልከቻ ቅፁን በማህተሙ ማረጋገጥ፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ(1) እና (2) በተመለከተው መሰረት የሕንፃ ባለቤትነት ወይም የባለ ይዞታ ምስክር ወረቀት፣ የሕንፃ ውስጥ- ሕንፃዊንድፍ ወይም ፕላን፣ የሕንፃው የግንባታ ፈቃድ እና የሕንፃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ኮፒ ማቅረብ፤
4. በግንባታ ፈቃድ መሰረት ለሕንፃው ተፈፃሚነት ያለውን የተሽከርካሪ ማቆሚያ ደረጃ መስፈርቶችና ፍቃድ ባለውየ ሥነ-ሕንፃ ባለሙያ ወይም ድርጅት የተደረገ ልኬት መዘርዘር፤
5. በክፍያ የሚሠራ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ኮምፒውተራይዝድ የመረጃ ሥርዓት መኖሩን የሚያስገነዝብ ማስረጃን የሚያካትት የተሽከርካሪ ማቆሚያ በቴክኖሎጂ የተደገፈ መገልገያዎች ዝርዝር፤
6. ለአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ልዩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ማዘጋጀቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**14. የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አገልግሎት ክፍያ እና ዕድሳት**

1. **የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ፣ የመኖሪያ ቤት እና አካባቢ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እና የእድሳት የአገልግሎት ክፍያ በሚመለከተው አካል ክፍያ ደንብ መሠረት ይከፍላል፤**
2. **ማንኛውም የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተ ፍኬት የተሰጠው ሰው ሰርተፍኬቱ የሚያገለግልበት የመጨረሻው ቀን ቀጥሎ ባሉት ሰባት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን መስፈርቶችን በማሟላት ማሳደስ ይኖርበታል፡-**

**ሀ. የሚመለከተው አካል የእድሳት ማመል ከቻ ቅፅ በመሙላት መፈረምና በተሽከርካሪ ማቆሚያ መገልገያው ላይ የተደረጉ ለውጦች ሲኖሩ የተደረጉትን ለውጦች የሚያሳዩ ሰነዶችን ማቅረብ፣**

**ለ. አመልካች የማመልከ ቻቅፁን በማህተሙ ማረጋገጥ፤**

**ክፍል ሦስት**

**የተለያዩ አካላት ኃላፊነት**

**15. የሚኒስቴሩ ኃላፊነት፡**

1. መመሪያውን በማጽደቅ ወደ ስራ እንዲገባ ያደርጋል፡፡
2. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መመሪያ አተገባበር ላይ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡
3. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች ደረጃዎች ይወስናል አተገባበራቸውን ይከታተላል

**16. የአገልግሎቱ ኃላፊነት፡**

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው አካላት በተዘረጋው የአሰራር ስርአት መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ይከታተላል፡፡
2. ድንገተኛ ቁጥጥር በማድረግ ፈቃድ ሳይኖራቸው የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ አካላትን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ይህንን ባደረጉ አካላት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
3. ስለ መመሪያዉ አተገባበር ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡

**17. የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ/የሚመለከተው አካል/ ኃላፊነት**

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣሉ ያድሳሉ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ይሰርዛሉ፤
2. የመንገድ ዳር የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ የተደራጁ ማህበራት ጋር ውል ይዋዋላሉ፤
3. በመንግስት የለሙ ወይም ለተሽከርካሪ መቆሚያነት የተለዩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን ያስተዳድራሉ፤
4. የተሽከርካሪ መቆሚያ መሰረተ ልማት ብቁ መሆኑን አረጋግጠው አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋሉ፤
5. የመንገድ ዳር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን በልዩ የቀለም ምልክት ያደርጋሉ፤
6. የተሽከርካሪ ማቆሚያ የአገልግሎት ክፍያ ተመን በማጥናት ለመንግስት ያቀርባሉ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
7. የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በማሳተም ለማህበራቱ ያቀርባሉ አፈፃፀሙንም ይከታተላሉ፤
8. ማህበራት ተግባራቸውን በገቡት ውል መሰረት እየፈፀሙ ስለመሆናቸው ይከታተላሉ ይቆጣጠራሉ፣ ውሉን ጥሰው ሲገኙ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፤
9. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን የሚያመላክት የማስታወቂያ ሰሌዳ፣ አስፈላጊ የመንገድ ምልክት እና ማመላከቻዎች ለእይታ ግልፅ በሆነ ቦታ ያስቀምጣሉ፤
10. የመንገድ ዳር የተሽከርካሪ ማቆሚያዎችን ከአከባቢው የትራፊክ እንቅስቃሴ እና ለአደጋ ካላቸው ተጋላጭነት አንፃር በመገምገም ቦታውን ለጊዜው ወይም በቋሚነት አገልግሎት እንዳይሰጥ ሊያደርጉ ይችላሉ፤
11. ዘመናዊ የተሽከርካሪ መሰረተ ልማት የመድን ዋስትን እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡

*18.* **የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ኃላፊነት**

1. **የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባገኘ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ማቅረብና የጊዜ ሰሌዳውን ሲያሻሽል ማሻሻያው ስራ ላይ ከመዋሉ አምስት ቀን በፊት በፅሑፍ ያሳውቃል፤**
2. **ባዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል፤**
3. **የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ሰፍራ መግቢያና መውጫ በሮች ላይ ጎልቶ በሚታይ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወይም በተመሳሳይ መገልገያ ላይ ተደርጎለተገልጋዮች ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፤**

4. ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለተገልጋዮች ተደራሽለማድረግ አግባብ ባላቸው የትራፊክ ምልክቶች ተለይቶእንዲመላከት ያደርጋል፤
5. ቀድሞ የመጣ ተገልጋይ ቀድሞ እንዲ ስተናገድ ያደርጋል፤
6. በክፍያ ለሚገለገሉ ተገልጋዮች የተያዙናያል ተያዙ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ሥርዓት በመጠቀም አገልግሎት ይሰጣል፤
7. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተጠባበቀው በሚቆሙ ተሽከርካሪዎች እንዳይጨናነቅወይም ከመያዝ አቅሙ በላይ አገልግሎት እንዳይሰጥ ያደርጋል፤
8. ለተገልጋዮች ሕጋዊ ደረሰኝ በመስጠት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ክፍያ መሰብሰብና ለሚመለከተው አካል ካሳወቀው የክፍያ መጠን በላይ እንዲ ከፍሉ እንዳይደረግ ይቆጣጠራል፤
9. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ሠራተኛ የሚመለከተው አካል ባወጣው የደንብ ልብስ በስታንዳርዱ መሠረት አንጸባራቂ የደንብ ልብስ ለብሶ መገኘት ይኖርበታል፤
10. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት እየሰጠያ ለሠራተኛ  ንጽህናውን የመጠበቅ፤ከአስካሪ መጠጥ፣ ከአደንዛዥ ዕጽ እና መሰል አስነዋሪ ድርጊት የተቀጠ በመሆን አለበት፤
11. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታውና መገልገያው ፅዳትና ውበት በአግባቡ እንዲያዝና እንዲጠበቅ ያደርጋል፤
12. በተሽከርካሪ ማቆሚያው የሚገኝ ተሽከርካሪን ደህንነት የመጠበቅ ኃሊፊነት ይኖርበታል፤
13. ክትትል በማድረግ በተሽከርካሪ መቆሚያ ቦታው ባል ታወቀ ተገልጋይ የተተወ ተሽከርካሪ መኖሩን እንዳወቀ ለፖሊስ ወዲያውኑ በማሳወቅ ተሽከርካሪው ከቆመበት እንዲነሳ፣ እንዲጓጓዝና በፖሊስ ጥበቃስር እንዲውል ያደርጋል፤
14. በሚመለከተው አካልም ሆነ በሌሎች ባለድርሻ አካላት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ነክ መረጃ ሲጠየቅ ይሰጣል፤
15. በተገልጋዮች የሚቀርቡበትን ቅሬታዎች በመቀበል ፍትሐዊነትና አግባብነት ባለው መልኩ ያስተናግዳል፤
16. የአሽከርካሪነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለውን ሠራተኛ ጨምሮ ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል።

19. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራት ኃላፊነት

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማቱን ይረከባል፣በአግባቡ እና በጥንቃቄ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፤
2. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማቱ ውስጥ የሚገኙትንና የሚገለገሉበት ንብታዎችና መሳሪያዎች ይከታተላል፤ ጥበቃ ያደርጋል እንዲሁም ከሌሎች የጸጥታ አካላት ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፤
3. በሚመለከተው አካል የክፍያ እና ሂሳብ የስራ ክፍል በሚቀርብላቸው ገንዘብ መሰብሰብያ ደረሰኝ የተሽከራካሪ ማቆሚያ ክፍያ ይሰበስባል፣
4. የተሽከርካሪ ማቆሚያ የአገልግሎት ክፍያ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በመንግስት የክፍያ አሰራር ስርዓት መሰረት ይሰበስባል፤

5. በየቀኑ የተሰበሰበውን የአገልግሎት ክፍያ በውሉ መሰረት የሚጠበቅበትን ሂሳብ በቀኑ ወደሚመለከተው አካል የባንክ ቁጥር ገቢ ያደርጋል፣ በእሁድና በሌሎች የባዕላት ቀናት ባንክ ዝግ በሚሆኑበት ጊዜ በሚቀጥለው የስራ ቀን ገቢ ያደርጋል፤
6. የባንክ ገቢ ደረሰኝ ከገቢ በኋላ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤
7. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማት ጽዳት እና ውበት የመጠበቅ ተግባራት ያከናውናል፤
8. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች በተሽከርካሪያቸው ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ንብረት ከስርቆት ለመጠበቅ እንዲቻል እንዲያስመዘግቡ በማስታወቂያ የማሳወቅና የተመዘገበ ንንብረት የመጠበቅ ግዴታ ይኖርበታል፤
9. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማቱን በውሉ መሰረት በአግባቡ ማስተዳደር በሚችሉ የተለያየብቃት ባላቸው ሙያተኞች የተደራጀ እንዲሆን ያደርጋል፤
10. የገቢና የወጪ ደረሰኞች እንዲሁም አስፈላጊ ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፣ሪፖርትያደርጋል፤
11. የሚመለከተው አካል በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረት የአገልግሎቱን ከንውን በየሳምንቱ ሪፖርት ያቀርባል፤
12. ከተጠቃሚው የአገልግሎት እርካታ መረጃ በመሰብሰብ ተገልጋዩን ለማርካት የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራሩን ያሻሽላል፤
13. በኃላፊነት የተረከቧቸውን ንብረቶች በማንዋል እና በአጠቃቀም መመሪያ መሰረት መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፤
14. በሀላፊነት የተረከባቸውን ንብረቶች ሲበላሹ ለሚመለከተው አካልማሳወቅ ይጠበቅበታል፤
15. በተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት ላይ የሚከናወኑ የማስታወቂያ ስራዎች ከሚመለከተው አካል ጋር በሚገባው ውል መሰረት ገቢ ያደርጋል፤
16. የማስታወቅያ ስራ ሊያከናውን ከሚመለከተው አካል ጋር በቅድሚያ ስምምነት መድረስ ይጠበቅበታል፤

20.**የተገልጋይኃላፊነት**

1. **በጊዜ ሰሌዳውና በተቀመጡለት ሌሎች መስፈርቶች መሰረት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መጠቀም፤**
2. **ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ተብሎ በተወሰነውና ለጊዜው በሚሰጠው ቦታ ብቻ ተሽከርካሪውን ማቆም፤**
3. **በክፍያ ለሚያገኘው የተሽከርካሪ ማቆም አገልግሎት የአገልግሎት ክፍያ መፈፀም፤**
4. **ከሚመለከተው አካል የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ወይም ከትራፊክ ተቆጣጣሪ ጋር የመተባበር።**

**21. የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሀላፊነት**

በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ላይ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ስርዓት ያስከብራል ወይም ይቆጣጠራል

**22. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለው ማናቸውም ሰው ኃላፊነት**

1. ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ለተገልጋዮች ተደራሽ በሆነ መልኩ አግባብ ባላቸው የትራፊክም ልክቶች ተለይቶ እንዲመላከት ማድረግ፤
2. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ባገኘ በሰባት ቀን ውስጥ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ማቅረብና የጊዜ ሰሌዳውን ሲያሻሽል ደግሞ ማሻሻያው ስራ ላይ ከመዋሉ አምስት ቀን በፊት ለሚመለከተው አካል በፅሑፍ ማሳወቅ፤

3. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ስፍራ መግቢያና መውጫ በሮች ላይ ጎልቶ በሚታይ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወይም በተመሳሳይ መገልገያ ላይ ተደርጎ ለተገልጋዮች ይፋ እንዲሆን ማድረግ፤
4. ባዘጋጀውና በሚመለከተው አካል ባሳወቀው የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ቀድሞ የመጣ ቀድሞ እንዲስተናገድ በማድረግ አገልግሎት መስጠት፤
5. በክፍያ ለሚገለገሉ ተገልጋዮች የተያዙና ያልተያዙ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን ኮምፒተራይዝድ የመረጃ ስርዓት በመጠቀም አውቀው ቦታ እያለየለም ተብለው አገልግሎት እንዳይነፈጉ፤ማድረግ፤
6. ለተገልጋዮች ሕጋዊ ደረሰኝ በመስጠት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ክፍያ መሰብሰብና ለሚመለከተው አካል ካሳወቀው የክፍያ መጠን በላይ እንዲከፍሉ እንዳይደረግ ያደርጋል፤
7. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታውና መገልገያው ፅዳትና ውበት በአግባቡ እንዲያዝና እንዲጠበቅ ያደርጋል፤
8. በተሽከርካሪ ማቆሚያው የሚገኝ ተሽከርካሪን የመጠበቅ ኃላፊነት ይኖርበታል፤
9. ክትትል በማድረግ በተሽከርካሪ መቆሚያ ቦታ ውባልታወቀ ተገልጋይ የተተወ
ተሽከርካሪ መኖሩን እንዳወቀ ለትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ወዲያውኑ በማሳወቅ ተሽከርካሪው ከቆመበት እንዲነሳ፣ እንዲጓጓዝና በትራፊክ ፖሊስ ጥበቃ ስር እንዲውል ያደርጋል፤
10. በሚመለከተው አካል እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ነክ መረጃ ሲጠየቅ ይሰጣል፤
11. በተገልጋዮች የሚቀርቡለት ንቅሬታዎች በመቀበል ፍትሐዊነትና አግባብነት ባለው መልኩ ያስተናግዳል፤
12. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለውን ሰራተኛ ጨምሮ ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን ይቀጥራል፤
13. የተገልጋይ አገልግሎት እርካታ ምዘናዎችን በተከታታይ በማካሄድ በሚገኘው ውጤት መሰረት ማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

## ክፍል አራት

## ቅጣት እና ክልከላ

### 23. ክልከላ

1. በመንግስት የለሙ የተሽከርካሪ ማቋሚያ አገልግሎት

ሀ) ማንኛውም ማህበር/ድርጅት ከሚመለከተው አካል ጋር የአገልግሎት ውል ሳይፈፅም ወይም የፈፀመው ውል ሳይታደስ የተሽከርካሪ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

ለ) ማህበራት/ድርጅቶች ያለ ደረሰኝ ወይም ከሚመለከተው አካል እውቅና ያልሰጠው ደረሰኝ ወይም የሚመለከተው አካል ካዘጋጀው ደረሰኝ ውጪ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ክፍያ መሰብሰብ የተከለከለ ነው፡፡

ሐ) የማህበር አባልነትን የሚገልፅ የሚመለከተው አካል ከሚያስቀምጠው ስታንዳርድ ውጪ ለብሰው የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

መ) ከሚመለከተው አካል ውል ገብቶ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰሩ ማህበር አባል ውጪ ለሶስተኛ አካል ማስተላለፍና ቀጥሮ ማሰራት የተከለከለ ነው፡፡

ሠ) ማህበራት ወይም የግል ድርጅት ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የተረከበውን ስፍራ እና መሳሪያዎች ከአላማው ውጪ ለማንኛውም አይነት የንግድ ስራ ወይም ለሌላ ተግባር ማዋል የተከለከለ ነው፡፡

ረ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ እና መሳሪያዎች ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ የተከለከለ ነው፡፡

ሰ) ያለአግባብ ገቢ ለማግኘት ሲባል የክፍያ ማሽን ማበላሸት ወይም የተሳሳተ ክፍያ እንዲወጣ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

ሸ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ እያለ አገልግሎት መከልከል፣ የአገልግሎት ታሪፍ መደበቅ እና ከታሪፍ በላይ ሂሳብ ማስከፈል የተከለከለ ነው፡፡

ቀ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሰዓት አለማክበር፣ ከአቅም በላይ ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ ማድረግ፣ ተጠቃሚዎችን በቅደም ተከተል እና በአግባቡ አለማስተናገድ የተከለከለ ነው፡፡

2. በግል የተሽከርካሪ ማቋሚያ ስፍራ አገልግሎት

ሀ) ማንኛውም የግልየተሽከርካሪ ማቋሚያ ስፍራ አገልግሎት ከሚመለከተው አካል የብቃት ማረጋገጫ ሳያገኝ ወይም ወቅቱን ጠብቆ ሳያሰድስ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

ለ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራን አጠቃቀም ማዛባት ወይም የሕንፃ ማቆሚያ ስፍራን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለሌላ ዓላማ ማዋል የተከለከለ ነው፡፡

ሐ) የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ሰሌዳ አለማ ውጣት፣ የወጣውን የጊዜ ሰሌዳ ስራላይአለማዋል የተከለከለ ነው፡፡

መ) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለውን ጨምሮ ለተሽከርካሪ ማቆም አገልግሎት አሰጣጥ አግባብነት ያላቸው የቴክኒክ እና የፀጥታ ሰራተኞች በመደበኛነት ሳይመድብ እና የደንብ ልብስ እንዲለብሱ ሳያደርግ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

ሠ) ተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የክፍያ ተመን ማስታወቂያ ሳይለጥፍ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

3. ተገልጋይ

ሀ) ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዱ ሰሌዳ ሳይለጥፍ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ማግኘት የተከለከለ ነው፡፡

ለ) የሚመለከተው አካል በልዩ ሁኔታ ለዲፕሎማት ማህበረሰብ እና ለአካል ጉዳተኞች በለያቸው የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

ሐ) ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ያለመክፈል የተከለከለ ነው፡፡

**24. ስለ አስተዳደራዊ እርምጃ**

1. በወንጀል ሕግ እና በሌላ አግባብ ባለው ሕግ የሚኖረው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰድበታል፡-

ሀ)ማንኛውም ሰው በዚህ በመመሪያ አንቀጽ23 የተዘረዘሩትን ክልከላዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ፈጽሞ ከተገኘ ድርጊቱን እንዲያቆም ወይም እንዲያርም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

ለ) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ደርጊቱን መፈጸም ያላቆመ ወይም የእርምት እርምጃ የማይወስድ ሆኖ ሲገኝ የሚመለከተው አካል እንደ አግባብነቱ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ የተመለከተው አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፤

ሐ) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ወይም አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ባለመታረም የጥፋት ድርጊቱን መፈጸም የማያቆም ወይም የእርምት እርምጃ የማይወስድ የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት ወይም ማህበር ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይታገዳል፤

መ) የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱን ማገድ በቂ ሆኖ በማይገኝበት ጊዜ ወይም እግዱ በተሰጠበ 30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጥፋት ድርጊቱን በማቆም ወይም የእርምት እርምጃ በመውሰድ እግዱ እንዲነሳለት ካልጠየቀ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ይሰረዛል፣

ሠ) ጥፋት የፈጸመው ከሚመለከተው አካል ጋር ውል የተዋዋለ ማህበር ወይም የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ድርጅት በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ወይም አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ባለመታረም የጥፋት ድርጊቱን ካላቆመ ወይም የእርምት እርምጃ ካልወሰደ ውሉ ይሰረዛል፡፡

2. በዚህ መመሪያ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የሚመለከተው አካል በልዩ ሁኔታ ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ እና ለአካል ጉዳተኞች ወይም በልዩ ሁኔታ በለያቸው የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች ላይ የሚገለገል ተገልጋይ አግባብ ባለው የትራፊክ ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3. የሚመለከተው አካል የክትትል ባለሙያዎች ጥፋትፈጻሚዎችን በመለየትና አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎችን በማያያዝ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያቀርባል፤
4. የሚመለከተው አካል በዚህ መመሪያ ላይ የተከለከለ ተግባርለፈጸመው ማህበር ወይም የግል ድርጅትየቀረበበትን ክስ በጽሁፍ በማሳወቅ መልስ ይዞ እንዲቀርብ ጥሪ ያደርጋል፣
5. ጥሪ የደረሰው ማህበር ወይም የግል ደርጅት ጥሪው በደረሰው አምስት ቀናት ውስጥ መልሱን በጽሁፍ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ የሚመለከተው አካል ጉዳዩን መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. የሚመለከተው አካል የመንገድ ዳር የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች የአገልግሎ ክፍያ ተመን፣ የማህበራትን እና የመንግስት ድርሻ መጠን፣የማህበራትን አሰራር እና አደረጃጀት የተሽከርካሪ ማቆሚያ የአስተዳደር አይነት እና ሁኔታ የቅጣት ዓይነትና መጠን ሊወስን ይችላል፡፡

## 7. ስለቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

1. ማናቸውም ቅሬታና አቤቱታ አቅራቢ በመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎቱን ለሰጠው የሥራ ክፍል በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤ ቅሬታው የቀረበበት የስራ ክፍል ለቀረበው ለአቤቱታ በ (አምስት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ምላሽ መስጠት አለበት፤
2. ቅሬታው የቀረበበት የሥራ ክፍል በሰጠው ምላሽ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው አካል ዋና ኃላፊ ይሆናል፤
3. አቤቱታ የቀረበለት የሚመለከተው አካል ዋና ኃላፊ አቤቱታው በቀረበለት በ5(በአምስት) የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ ይሰጣል፤የሚመለከተው አካል የበላይ ኃላፊ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

ክፍል አምስት

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

25 . የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

26. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

27. መመሪያ ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

28. መመሪያ ውስ ለሚፀናበት ጊዜ

ይህመመሪ የከ….ቀን/2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ዶ/ር ዓለሙ ስሜ**
**የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚንስቴር ሚኒስትር**

አስተዳደራዊ ቅጣት ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የጥፋትአይነቶች | አስተዳደራዊየቅጣትመጠን |
|---|---|---|
| 1 | የሕንፃ የተሸከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫምስክርወረቀት ሳያሳድሱአገልግሎትመስጠት፤ | አንድመቶሺህብር (100,000ብር) |
| 2 | የሕንፃ የተሸከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ አጠቃቀምን ማዛባት ወይም የህንፃ ማቆሚያ ስፍራን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለሌላ አላማ ማዋል | አንድመቶሺህብር (100,000ብር) |
| 3 | በክፍያለሚሰሩአገልግሎቶች መንጃ ፈቃድ ያለውን ጨምሮ የሕንፃውተሸከርካሪ ማቆምያ አገልግሎትአሰጣጥ የቴክኒክ እና የፀጥታሰራተኞችበመደበኛነትአለመመደብ | ሶስትሺህብር (3,000ብር) |
| 4 | በክፍያለሚሰሩአገልግሎቶችየሕንፃ ማቆሚያ አገልግሎት የቴክኒክወይም የፀጥታ ሠራተኛ የደንብልብስእንዲለብሱአለማድረግ፤ | ሶስትሺህብር (3,000ብር) |
| 5 | የግልተሸከርካሪማቆሚያ ድርጅት ወይም ማህበራት የቴክኒክ ወይምየጥበቃ ሠራተኛ አንጸባራቂ የደንብልብስያልለበሰ፤ | አንድሺህአምስት መቶብር (1,500ብር) |
| 6 | ግልፅና ወጥነት ያለው የሕንፃ የተሸከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎትየክፍያ ስርዓት እንዲኖር ወይምእንዲዘረጋአለማድረግ፤ | አስርሺህብር (10,000ብር) |
| 7 | በክፍያ ለሚሰሩ አገልግሎቶች የሕንፃ የተሸከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችንበቴክኖሎጂ የመረጃ ስርዓትን ስራ ላይአለማዋል፤ | አስርሺህብር (10,000ብር) |
| 8 | የብቃት የምስክር ወረቀት ሳያወጡየሕንፃየተሸከርካሪማቆምአገልግሎትመ ስጠት፤ | መቶሺህብር (100,000ብር) |
| 9 | የሕንፃየተሸከርካሪማቆሚያአገልግሎት አሰጣጥየጊዜሰሌዳአለማውጣትወይምየወጣውንስራላይአለማ ዋል፤ | አስር ሺህብር (10,000ብር) |